# ቅድመ ትምህርት ቤት መዋለ ሕጻናት

**የወላጆች መረዳጃ ማህበር ቅድመ ትምህርት ቤቶች**

በአካባቢ የማህበረተሰብ ወይም የቴክኒክ ኮሌጆች እርዳታ በወላጆች የተቋቋሙና የሚካሄዱ ለትርፍ ያልቆሙ ትምህርት ቤቶች።

- በዋሽንግተን የሚገኝ ሕጋዊ መልክ ያለው መዋለ ሕጻናት፡ ነገር ግን የሚሰጡት አገልግሎት ከአራት ሰዓት የበለጠ ካልሆነ በስተቀር የሥራ ፈቃድ ከማውጣት ነፃ ናቸው።
- በሕብረተሰብና ጤና አገልግሎት ጽ/ቤት ወይም በሕዝብ ትምህርት ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ማድረግ ይችላሉ።
- ወላጆች አስተማሪው‑ን/አስተማሪዋን በመርዳት ላይ በተራ ተካፋይ መሆን ይችላሉ።
- ወላጆች ከአስተማሪዎቹና ከኮሌጁ አስተማሪዎች ጋር ወርሐዊ የማታ ጊዜ ስብሰባ ላይ ይካፈላሉ።
- አንዳንድ ፕሮግራሞች የሥራ ፈቃድ ከማውጣት ነፃ ናቸው።
- የግማሽ ቀን ቅድመ ትምህርት ቤቶች
- ዕድሜያቸው ሁለት ዓመትና ከስድስት ወር እስከ ስድሰት ዓመት ለሆናቸው ልጆች በተለይ ምድብ የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት።
- አብዛኛውን ጊዜ በቀን ከሦስት እስከ አራት ሰዓት ለሥራ ክፍት ነው።
- በትክክል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ክፍለ ጊዜ ይከተላሉ።

**ሞንተሰሪ**

- ትምህርት ነክ ፍልስፍና- ይህ ልጁ/ጅቷ በራሱ ወይም በራሷ የተፈጥሮ ችሎታ ውድድር በሌለበት ሁኔታ መማር እንዲችል/እንድትችል ሆኖ የተዘጋጀ ነው።
- የአስተማሪው ድርሻ  እንደ መሪ በመሆን ለእያንዳንዱ ልጅ መማሪያዎችን ማቅረብና አስፈላጊም ሲሆን እርዳታ ማድረግ ነው።
- ከ3-5 ልጆችን መርዳትና ከ9:00-3:00 በሥራው ላይ መቆየት።

**ሄድስታርት**

- በፌደራል መንግስት የሚረዳ ፕሮግራም
- የትምህርት፡ የጤና፡ የምግብና የሕብረተሰብ አገልግሎቶችን አነስተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች ያቀርባል።
- በአንድ ትምህርት ቤት ዓመታዊ የትምህርት ክፍለ ጊዜ መሠረት አገልግሎት ይሰጣል።
- የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት/ትምህርት በቀን ለ3 1/2 ሰዓት 4 ቀናት በሳምንት አገልግሎት ይቀርባል።
- ኢሲኢኤፒ (ቅድመ የልጅነት ጊዜ ትምህርትና የእርዳታ ፕሮግራም) ከሄድስታርት ጋር የተመሳሰለ ነው። በስቴቱ የሚረዳና የሚመረና ነው።

**የጨዋታ ቡድኖች**

- በቤተሰቦች ቡድን የተዘጋጀ መደባዊ ያልሆነ ዝግጅት

**የሥራ ፈቃድ ያለው ቅድመ ትምህርት ቤት**

- የሥራ ፈቃድ ባለው መዋለ ሕጻናት ወይም የቤተሰብ መዋለ ሕጻናት ቤቶች አጥር ገቢ ውስጥ የሚደረግ።
- በቀኑ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ፡ ከፕሮግራሙ በፊትና በኋላ ሰፋ ያለ የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት።

**በተጨማሪም ይመልከቱ**

- ስለ የሥራ ፈቃድ
- ቤተሰቦችና ጓደኞች
- ሞግዚት
- መድሐኒት ከመኖሪያ ቤት ርቀው ሳሉ
- የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት አቅራቢ መፈለጊያችንን ይሞክሩ